# የሚያስመልጥ የፀሎት ጉልበት

*“ቶሎ ወደዚያ ሸሽተህ አምልጥ ወደዚያ እስክትደርስ ድረስ ምንም አደርግ ዘንድ አልችልምና”። ዘፍ 19፡22*

ይህን የተናገረው ሎጥን ለማውጣት በዚያ የነበረው መልአክ ነው። ምን ነበር እግዚአብሔር ሎጥን ከከተማይቱ እስኪያመልጥ ድረስ እንዲጠብቅ ያስገደደው? ጥቂት ቁጥሮች ዝቅ ብሎ ምክንያቱን እናገኘዋለን።

አብርሃምም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ወደነበረበት ስፍራ ለመሄድ ማልዶ ተነሳ ፣ ወደ ሰዶምና ወደገሞራ በዚያች ወዳለውም ምድር ሁሉ ተመለከተ፤ እነሆም የአገሪቱ ጢስ እንደ እቶን ጢስ ሲነሳ አየ። እግዚአብሔር እነዚያን የአገር ከተሞች ባጠፋ ጊዜ አብርሃምን አሰበው ፣ ሎጥ ተቀምጦበት የነበረውንም ከተማ ባጠፋ ጊዜ ከዚያ ጥፋት መካከል ሎጥን አወጣው።

ዘፍ 19፡28-29

“ቶሎ ወደዚያ ሸሽተህ አምልጥ ወደዚያ እስክትደርስ ድረስ ምንም አደርግ ዘንድ አልችልምና”። ዘፍ 19፡22

አብርሃምም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ወደነበረበት ስፍራ ለመሄድ ማልዶ ተነሳ ከሚለው ሀረግ አብርሃም ከዚህ ቀደም በእግዚአብሔር ፊት በምልጃ ጸሎት ቆሞ እንደነበር እንገነዘባለን። ታሪኩን ወደ 18ኛው ምዕራፍ ዞር ብለን መመልከት ያሻናል። “ሰዎቹም ከዚያ ተነስተው ወደ ሰዶም አቀኑ አብርሃም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሄደ። እግዚአብሔርም አለ፤-“ እኔ የማደርገውን ከአብርሀም እሰውራለሁን? ….. እግዚአብሔርም አለ፤- የሰዶምና የገሞራ ጩኸት እጅግ በዝቶአልና፣ ኃጢያታቸውም እጅግ ከብዳለችና፣ እንግዲህስ ወደ እኔ እንደ መጣች እንደጩኸትዋ አድርገው እንደሆን ወርጄ አያለሁ፤ እንዲሁምባይሆን አውቃለሁ። ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ፤ ወደ ሰዶምም ሄዱ፣

አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር”።ዘፍ 18፡22

አብርሃም ይህን ከመስማቱ አስቀድሞ እነዚህ ሶስት ሰዎች ወደቤቱ እንደመጡና በሚመጣው ዓመት ሳራ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ታላቅ የምሥራች የነገሩት ሲሆን በሰማው ነገር ተደስቶ ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሲወጣ ደግሞ ይህን ከላይ ያነበብነውን ፍርድ እግዚአብሔር ነገረው። አብርሃም ወደቤቱ ለመሄድ ለመደሰት በቂ ምክንያት ነበረው፣ የዘመናት ጸሎቱ ተመልሶለታልና።ከዚህም በላይ በነዚህ ከተሞች የሚያውቀው ሰው ቢኖር ሎጥን ብቻ ነው። ለዚያውም ሎጥ ወደዚያ የሄደውም በገዛ ምርጫው ነበር ታዲያ እነዚህን ምክንያቶች በመዘርዘር ምን ቸገረኝ ለማለትና ላለመጸለይ ምክንያት ለመስጠት ይችል ነበረ። ግን ከርሱ ደስታ ይልቅ የሰማውና ሊመጣ ያለው ፍርድ ከብዶ ስለታየው በእግዚአብሔር ፊት መቆሙን (መማለዱን) እንደመረጠ እናያለን ያውም ለሎጥ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ሊመጣባቸው ላሉት ለሁለቱም ከተሞች ለሰዶምና ለገሞራ እንጂ ። ጻድቅ በእግዚአብሔር ፊት ከቆመ እግዚአብሔር ስለእርሱ ሲል ምህረት እንደሚያደርግ አብርሃም በደንብ የተረዳ ሰው ነበር።



ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አላገኘሁም”።ሕዝ 22፡30

እንደ አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ቆመው የሚማልዱ አስር ጻድቃን በከተማይቱ ባይገኙም አንድ ጻድቅ ራሱን ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ።

ስለዚህ እግዚአብሔርን ሲጠይቀው እንዲህ አለ፦ በከተማይቱ ሀምሳ ጻድቃን ቢገኙ ስለነርሱ ብለህ ከተማይቱን አትምርም ወይ?

እግዚአብሔር መልሶ በፊቴ የሚቆሙ ሃምሳ ጻድቅ ቢገኙ ስለነርሱ ስል ከተማይቱን

እምራለሁ አለው። አብርሃም አርባ አምስት ቢኖሩስ፣ አርባ ቢኖሩስ፣ እያለ በመጨረሻ

ጌታዬ አይቆጣ አንድ ጊዜ ብቻ ልናገር አስር ብቻ ቢገኙስ? እያለ ስለከተማይቱ ከእግዚአብሔር

ጋር ተሟገተ ። እግዚአብሔርም ስለአስሩ ስል አላጠፋትም ብሎ መለሰለት። የሚገርመው ነገር

በከተማው አስር ጻድቃን እንኳን ያለመገኘታቸው ነው። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ንግግሩን

ከጨረሰ በኋላ ሄደ።፡

እንደ አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ቆመው የሚማልዱ አስር ጻድቃን በከተማይቱ ባይገኙም አንድ ጻድቅ ራሱን ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ።

> *“ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አላገኘሁም”። ሕዝ 22፡30*

ስለዚህ እግዚአብሔር ከተማይቱ ላይ ፍርድን ባደረገ ጊዜ በፊቱ የቆመውን ጻድቅ አብርሃምን አሰበው፣ ስለርሱም ፀሎት ሲል ሎጥን ከጥፋት ከተማ አወጣው ።

ዛሬ በዘመናችን በእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ ስራ ፃድቃን የሆንን እኛ ነን በእግዚአብሔር

ፊት ለምልጃ እንድንቆም የምንጠበቀው። በስሙ የተጠሩ ሕዝቡ በሰፍራቸው ሆነው በጸሎት

ቢተጉ ጌታ ስለሕህዝቡ ጸሎት ሲል ምህረት የሚያደርግ ነፍሳትን የሚያድን መሆኑ

ለስንቶቻችን ግልጽ ሆኖ ይሆን? ስንቶቻችንስ ሀላፊነታችን እንደሆን ተረድተን ይሆን?

ሰይጣን ጻድቅ በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም የሚሆነውን ስለሚያውቅ ባለው ሀይል ሁሉ

እንዳንጸልይ ይዋጋናል። ከዚህ የተነሳ ጸሎታችን ትግል የሞላበት ሆኗል። ከዚያም ሌላ

በተንበረከክን ቁጥር ጸሎታችን በራሳችን ችግር ዙሪያ ብቻ መሆኑ ደግሞ በተጨማሪ

አቅመቢስ አድርጎናል።እግዚአብሔር ከአብርሃም ጸሎት የተነሳ ሎጥን ከተፈረደባት

ከተማ እንዳወጣው አኛም ሰዎችን ከጥፋት ከተማ የሚያስመልጥና እግዚአብሔርን

ከፍርድ የሚያዘገየው ጉልበት ያለው ጸሎት ልንጸልይ እንደምንችል አውቀን እንድንነሳ

ያስፈልጋል። እግዚአብሔር በፈረሰው በኩል የሚቆም ቢገኝ ቢኖር ለምህረት ዝግጁ ነው፤

ግን ሰው ፈለግሁ አጣሁም ይላል። ይህ ሁሉ ሰው እያለ! እንዴት እግዚአብሔር ሰው አጣሁ

ይላል? እንል ይሆናል። አዎ እግዚአብሔር የጸሎት ሰዎች ችግረኛ ነው። ወገኖቼ ለዚህ

ለጌታ ጥሪ ምን ምላሽ እንስጥ? ዛሬውኑ እንነሳና የራሳችንን ነገር ረስተን ለሚጠፉት

መማለድ እንለማመድ።

የፃድቅ ሰው ጸሎት በስራዋ ሀይልን ታደርጋለች።

